# የተካፋይነት ደንቦች የቃላት ጥያቄዎች ፡ ሁለት

## የቃላት ጥያቄዎች

1. አንድ የኩኪስ ፋብሪካ 7,180 ኩኪሶችን አመረተ ። የተመረቱትን ኩኪሶች እኩል መጠን በሚይዙ ካርቶኖች ውስጥ ካደረገ በኋላ ፋብሪካው ምንም ተጨማሪ ኩኪሶች አልነበረውም። ፋብሪካው በእያንዳንዱ እሽግ ውስጥ ስንት ኩኪሶች ሊያስገባ ይችላል?

   ሀ) 3 ለ) 6 ሐ) 4 መ) 9

2. አንድ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ 8,000 ጫማዎችን በተለያዩ የጫማ ሳጥኖች ውስጥ እኩል ብዛት ያላቸውን ጫማዎች ለማስቀመጥ እና ለመደርደር የጫማ ሳጥኖቹ ውስጥ ምን ያህል ጫማዎች ሊኖሩ ይችላሉ?

   ሀ) 3 ለ) 6 ሐ) 9 መ) 10

3. ብሬ እና ታናሽ ወንድሙ በ 48 ጠጠሮች ገበጣ እየተጫወቱ ነው። ሁሉንም 48 ጠጠሮች በእያንዳንዱ የገበጣ ጉድጓድ ውስጥ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን ጠጠሮች ማስገባት ቢኖርባቸው ገበጣው ስንት ጉድጓዶች ሊኖሩት ይገባል?

   ሀ) 7 ለ) 6 ሐ) 5 መ) 9

4. አንድ አርሶ አደር ከማሳው ላይ 387 የስኳር ድንቾችን በተለያዩ ከረጢቶች በመክተት በገበያ ላይ ለመሸጥ ፈልጓል፡፡ ምንም አይነት ጣፋጭ ድንች ሳይኖር በእያንዳንዱ ከረጢት ውስጥ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን ድንች ለማስቀመጥ በእያንዳንዱ ቦርሳ ውስጥ ስንት ጣፋጭ ድንች ማስቀመጥ ይችላል?

   ሀ) 4 ለ) 8 ሐ) 3 መ) 5

5. በቮሊቦል ውድድር 93 ተጫዋቾች ገብተዋል። እያንዳንዱ ቡድን ተመሳሳይ የተጫዋቾች ቁጥር አለው። እያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ስንት ተጫዋቾች ሊኖሩ ይችላሉ?

   ሀ) 2 ለ) 4 ሐ) 3 መ) 10

LIVEWORKSHEETS

6. አንዲ 250 የሰላምታ ካርዶችን ለመሸጥ ሠራች። በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ተመሳሳይ የካርድ ብዛት እና ምንም ካርዶች ሳይቀሩ ካርዶቹን በሳጥን እያሸገች ትሸጣለች  አንዲ በእያንዳንዱ ሳጥን ውስጥ ስንት ካርዶችን ማስቀመጥ ትችላለች?

ሀ) 4 ለ) 6 ሐ) 5 መ) 9

7. በአንድ የጥያቄ ትዕይንት ላይ 924 ጥያቄዎች አሉ። እያንዳንዱ ምድብ ተመሳሳይ የጥያቄዎች ብዛት አለው። በዝግጅቱ ላይ ስንት ምድቦች ሊኖሩ ይችላሉ?

ሀ) 5 ለ) 9 ሐ) 6 መ)10

8. ባለሱቅ ሽምሱ የሰበሰበውን 90 እንቁላሎች ለመሸጥ ምንም እንቁላሎች ሳይቀሩ እንቁላሎቹን በቅርጫት ውስጥ አስቀምጧል ። በእያንዳንዱ ቅርጫት እኩል እኩል እንቁላሎች ቢያስቀምጥ በእያንዳንዱ ቅርጫት ውስጥ ስንት እንቁላል ማስቀመጥ ይችላል?

ሀ) 3 ለ) 5 ሐ) 10 መ) ሁሉም

9. አንድ የመኪና አከፋፋይ  6,945 አዳዲስ መኪኖች አስጭኗል። በእያንዳንዱ ቀለም ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው መኪናዎች ቢኖሩ ምን ያህል የተለያየ ቀለም መኪናዎች ሊኖሩ ይችላሉ?

ሀ) 10 ለ) 9 ሐ)  4 መ) 3

10. አንድ ድርጅት 5,148 የማስታወቂያ በራሪ ወረቀቶችን አሳትሞ በድርጅቱ ውስጥ ለሚገኙ የሽያጭ ሰራተኞቹ እኩል እኩል ቢሰጥ በድርጅቱ ውስጥ ምን ያህል የሽያጭ ሰራተኞች ይገኛሉ?

ሀ) 5 ለ) 8 ሐ)  7 መ) 3

11. በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ለሚከናወን የወላጆች ኮሚቴ የምርጫ ፕሮግራም ላይ 648 ተማሪዎች ተሳትፈዋል ፡፡ እያንዳንዱ ተመራጮች እኩል እኩል የመመረጥ እድል ያገኙ ቢሆን ምን ያህል የወላጅ ኮሚቴ አባል ተመርጠዋል ?

ሀ) 10 ለ) 5 ሐ)  7 መ) 8

LIVEWORKSHEETS

12. ሚኪያስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትቤት ወቅት የተነሳቸውን 9,531 ፎቶግራፎች በተለየዩ እረድሮች ለመደርደር ፈልጓል ፡፡ በእያንዳንዱ እረድፍ እኩል እኩል ፎቶግራፎችን ቢደረድር ሚኪያስ በስንት እረድፍ ፎቶግራፎቹን ማስቀመጥ ይችላል ?

ሀ) 9 ለ) 3 ሐ) 6 መ) ሀ እና ለ

13. አንድ ድርጅት ውስጥ 3318 ሰራተኞች ይገኛሉ ፡፡ ድርጅቱ ያሉትን ሰራተኞች በተለያየ የፈረቃ ስራ ለመመደብ ቢፈልግ እና በእያንዳንዱ ፈረቃ እኩል ሰራተኞችን ለመመደብ ድርጅቱ ስንት ፈረቃ ሊኖረው ይችላል?

ሀ) 9 ለ) 3 ሐ) 6 መ) ለ እና ሐ

14. ሄለን ያሏትን 695 አባባዎች ለተለያዩ ሱቆች እኩል እኩል ማከፋፈል ፈልጋለች፡፡ ሄለን ምንም አበባ ሳይተርፋት አከፋፍላ ለመጨረስ ብትፈልግ ለምን ያህል ሱቆች ማከፋፈል ትችላለች?

ሀ) 4 ለ) 3 ሐ) 5 መ) 7

15. ባለፈው ዓመት አንድ የማስቲካ ፋብሪካ የተለያዩ ጣዕም ያላቸው 3,894 የማስቲካ እሽጎችን አምርቷል ፡፡ እያንዳንዱ ጣዕም እኩል እኩል እሽግ ቢኖረው ባጠቃላይ ስንት ዓይነት የተለያዩ ጣዕሞችን ማምረት ይችላል ?

ሀ) 6 ለ) 3 ሐ) 2 መ) ሁሉም

LIVEWORKSHEETS